# ቀዩ መስመር እንዳይጣስ

## ከአሲምባ የውይይት መድረክ የተሰጠ መግለጫ

የአሲምባ የውይይት መድረክ የተቋቋመበት ዋና ዓላማ ባለፉት አርባ ዓመታት ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍትኃዊ ነፃነት ሲታገሉ ለወደቁ ፤ በደርግ ፋሺሽታዊ ሥርዓት በቀይ ሽብር ሠለባ ለሆኑ ፤ ለሕዝባችን ነፃነት እንታገላለን በሚሉ ጠባብ ብሔረትኞች ለተጨፈጨፉ ፤ በፅናታቸው ፤ በኢትዮጵያዊነታቸው ተግዘው ለማቀቁና አሁንም በየጉድባው አሣራቸውን ለሚቆጥሩ ፤ ከምድረ-ገጽ ደብዛቸው ለጠፉ የቁርጥዬ ቀን የኢትዮጵያ ጀግኖችና በዓለም ዙሪያ ካለውዴታቸው ተሰደው ለሚኖሩ ታጋዮች መታሰቢያ እንዲሆን ነው። መድረኩ በኢሕአፓ ውስጥ ለኢትዮጵያ ሕዝብ እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ መብት ሲታገሉ የተሰዉ ጓዶቻችን የተሰዉበትን ዓላማ ክቡር ነው ብሎ ያምናል። ከሁሉም በላይ አሲምባ አዲሱ ትውልድ ለሚጠብቀው መራራ ትግል ፤ ሊመረምረውና ሊማርበት የሚገባ ፤ በዛሬዪቱ ኢትዮጲያችን የተንሠራፋው የዘረኞች ፤ የጎጠኞችና ፤ የሆዳሞች መንጋ የሚከላልሰውን ፤ በጀግንነት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ባላቸው ፍቅር ፤ ለፍትኅና ለዲሞክራሲ ፤ በውድ ሕይወታቸው ምስወዕትነት ያዳበሩትን የዚያን ትውልድ ጅግኖች የትግል ታሪክ ፤ ሳይቀነስ ፤ ሳይበረዝና ሳይደለዝ ፤ አሁንም በሕይወታቸው ከሚኖሩ የትግል ጓዶቻቸው ፤ የሥራ ባልደረቦቻቸው ፤ ወዳጆቻቸውና ቤተ-ዘመዶቻቸው ተሰባስቦ ፤ ዕውነቱ በትክክል እንዲቀርብ ይታገላል። የእነዚህን ለህዝብ ነፃነት ዴሞክራሲ ሲታገሉ የወደቁትን ጓዶቻችንን የሚያራክሱ ታሪካቸውን ለማቆሻሸ የሚጥሩትን እስከመጨረሻው ይዋጋል። በየጊዜውና በየወቅቱ የእነዚህን ቆራጦች ታሪክ ለማበላሸት የተነሱትን በሙሉ የኢትዮጵያ ህዝብ እንዳዋረዳቸው የሚታወቅ ነው። ለትግል የአዘጋጃቸውንም ፓርቲ ኢሕአፓን ስሙን እስከመቀየር ድረስና በስሙ ሌላ ድርጅት ለማቋቋም የአደረጉት ሙከራ ሁሉ መክሸፉ የማይታበል ሃቅ ነው።

ትግል እየነጠረ ሲሄድ በአንድ ትግል የተሰለፉ ግለሰቦች በተለያየ ምክንያት ከትግል መድረኩ ይወርዳሉ ውይም የትግል አቋማቸውን ይቀያይራሉ። የትግል አቋማቸው ሲቀየር ደግሞ የትግል አጋራቸውም እንዲሁ። እንደዚህ ያለ ሂደት ደግሞ ሊያመጣ የሚችለውን ከዚህ በፊት የነበረውን መከፋፈል ከዛም ያደረሰውን ጭፍጨፋ ከታሪክ እንማራለን። ለግል ጥቅማቸው ሲሉ በደርግም ይሁን በወያኔ ዘመን ብዙዎቹ እኛ ኢሕአፓዎች ነን በማለት ትግሉን መሃል ላይ ለመሸጥ የተነሱ በሙሉ የደረሰባቸውን ሁላችንም የምናውቀው ነው።

ዛሬም ታዲያ በኢሕአፓ ውስጥ የተፈጠረውን በጥሞና እየተከታተልን ሲሆን እኛ በበኩላችን ደግሞ ቀዩ መስመር እንዳይጣስ በሚል ይህንን በግለጫ ለመስጠት ተገደናል።

ለብዙ ዘመናት በአንድ የትግል መድረክ ላይ አብረው ሲታገሉ ቆይተው አሁን ሲለያይ በሁሉም ላይ ይታይ የነበረው ሃዘን በለቅሶ ሲገለጽ እንደነበረ ሰሞኑን ሰምተናል። እኛም በኃዘን ሁኔታዎችን ስንከታተል ቆይተናል። በአስተሳሰብ ተለያይተው አንድ ላይ መሥራት አቅቶአቸው በመለያየታችው ብቻ ተወስኖ ሳይቀር አደባባይ አውጥተው ጭቃ ሲለጥፉ የጠላት አንጀት ቅቤ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ሌላ አንገት ማስደፊያ ሰቆቃውን ማራዘሚያ እንዲሆን ሲደረግ መመልከት ያስገረመንና ያሳዘነን መሆኑን በዚህ አጸያፊ ትግባር የተሠማሩ ሁሉ እንዲያውቁልን እንተልጋለን። ሁኔታው እያደር የሚጣራ ቢሆንም ገና ከጅምሩ ከታዩት መግለጫዎች እንዴት እንደምንሄድ ያስታውቃልና ነገ ምን ይጠብቀናል? እነዝህን ጓዶቻችንን ትተን አሁን የምናገኛቸው አዲሶቹ ጓዶቻችን እነማን ናቸው? ለብዙ ዘመናት ስናስታውሳቸው የነበሩትን ጓዶቻችንስ እነማን ልንላቸው በምን ልንፈርጃቸው ነው? ለብዙ ዘመናት ስናስታውሳቸው የነበሩትን ጓዶቻችንን አላማ እንደጠበቅን ምንም ሳናቋሽሽ እንዴት አዲስ ካባ ለብሰን መሄድ እንችላለን? እንዴትስ የኢትዮጵያን ሕዝብ ጥቅም የሚያስጠብቅ ትግል መቀጠል እንችላለን? ብሎ ማሰብ ተገቢ ነው። ሌላው ደግሞ እንዴት አድርገን ነው ታሪካችንን ከአሁን አቋማችን ጋር የምናስተካክለው? አዲሶቹን ጓዶቻችንስ ይህንን ይቀርበሉታል ውይ ብሎ ቆም ብሎ ማጤን ያስፈልጋል። አሊያ ግን የውሃ ላይ ኩበት ሆኖ መንሳፈፍ ይመጣል።

የትግል አቋም ሲቀየር የትግል አጋርም ይቀየራል። ከፉንጋዋ መሥራት አቃተኝ ብሎ ከአስቀያሚዋ ጋር እንዴት ነው መሥራት የምችለው ብሎ ማሰብ ብልህነት ነው። ዛሬ ለድርድር ተብሎ ድሮ በጠላትነት ፈርጀው ታግለው ሲያሳድዱን ለነበሩ ታማኝነታችንን ለመግለጽ ከበፊቱ አቋማችን ምኑን ያህል መቀየር አለብን ብሎ ማሰብ የግድ ይሏል። አለበለዚያ ግን ውጥረቱ በበዛ ቁጥር አቋም እንደሌለው ያንንም ያንንም አስደስታለሁ በማለት የድሮ የሞቱለትን ክቡርና አቋም መናድን ለድሮ ጠላት ተገዢ ሆኖ መገኘት ነው።

ሕይወያቸውን መስዋዕትነት ያደረጉ ፤ አብረው ለቆሙለት አላማ ያለፉትን ጓዶች በታሪክ ውስጥ ተጠያቂ ለማድረክ መቸኮል ምናልባት ዛሬ ልንቀርባቸው የምንሻቸውን የሞራል ድጋፍና ማካካሻ ትብሎ ይገመት ከሆነ ያስተዛዝብ እንደሁ እንጂ በደም የታነፀውን ታኪካቸውን ቅንጣት ያህል እንኳ አያቆሸሸውም።

ነገ በእንባ ከሸኙ ጓዶች ሲለያዩ አዲስ የሚጠብቋቸው ጓዶቻቸው ባወጡት ህግጋት ሳይሆን እነርሱ ለብዙ ዘመናት ሲወነጅሏቸው በነበሩነት ስለሚሆን በየወቅቱ ወደ እነርሱ ካምፕ ሙሉ በሙሉ ለምግባት ብዙ ጥያቄዎችን እንደሚያቀርብባቸው ጥርጥር የለውም። ማመን ተጀምሯልና መቀጠሉ አይቀርም። ምን ያህል ነው የምንሄደው ብሎም እራሳቸውን መጠየቅ አስፈላጊ ነው። ያተያዘውን አዲሱን አላማ ለማሳመን ስባል የኢሕአፓን ታሪክ ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ የተሳሳተ ነው ብሎ አዲስ አቋም መያዝ ድግሞ ምን አይነት አድርባይነት እንደሆነና ጠላቶቻችን እንኳ ሊያምኑት እንደማይችሉ ቢሆንም ግን ለፀረ ኢሕአፓነት ለቀይ ሽብር ትግባራቸው የሞራል ማካካሻ ሊጠቀሙበት እንደሚችሉ ግልፅ ነው።

ከሚገባው በላይ ደጋፊን ለመሰብሰብ ያህል ከዚህ በፊት ፓርቲውን ክደው የወጡቱ የተጠቀሙበትን መንገድ መጠቀም ብሕብረተሰቡ ውስጥ ምንም አይነት ቦታ እንደማያስገኝ ታሪክን ዞር ብሎ መመልከቱ ይበቃል እንላለን። ልግል ጥቅም ሲባል የንፁሃኑን የቆራጦችን ስም መበከል እንደሚያስጠይቅም ማሰብ ይኖርብናል።

የአሲምባ የውይይት መድረክ ኢሕአፓ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከሊቅ እስከ ደቂቅ በከፍተኛ ምስዋዕትነት በደም ባጥንቱ የገናባው ቅርስ ስለሆነ ማንም ሰው ብግልም ሆነ በቡድን ዛሬ የድርጅት አባልም እንኳ ቢሆን ሁለት ሶስት ኢሕአፓ የመፍጠር መብትም ሆነ የሞራል ብቃት ሊኖረው አይገባም በሎ ያምናል። የውስጥ ያሠራር ችግሮችም ሆነ ሌሎችም ኢሕኢፓ ዴሞክራሲያዊ አሰራር ስላለው እዚያው ድርጅቱ ውስጥ ማለቅ አለበት ብለን እናምናለን። ችግሮች በውይይት ለፈቱ ሲገባ መሸሸ ችግሮችን ያባብሳል እንጂ ሊኢትዮጵያ ሕዝብ ምንም እንደማይፈይድ መታወቅ አለበት። ስም ለማጥፋት መራወጥ ማንነትን ያጋልጣል እንጂ መፍትሄ አያመጣም ብለንም አናምንም

የአሲምባ የውይይት መድረክ ከላይ ያሳሰብነውን ዕውነታ ብፅሞና በማስተዋል ቀዩን መስመር አልፊው ለብዙ ዘመናት የታገሉለትን ክቡር ዓላማ በዕልህ የተሰዉ ጓዶቻችንን የሚያዋርድ ተግባር ላይ እንዳንሰማራ ከወዲሁ ቀዩ መስመር እንዳይጣስ በሚል ለማሳሰብ እንወዳለን።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ያቸንፋል!
ኢሕአፓ የኢትዮጵያ ቅርስ ነው!
እንድ ኢሕአፓ! አንድ ኢትዮጵያ! ኢትዮጵያዊነት ያለጥርጥር ያቸንፋል!

የአሲንባ የውይይት መድረክ